## ማን እንደሚያፈነዳ በርግጠኛነት በማስረጃ አስደግፎ ለእሁኑ መናገር ባይቻልም መቼ ቦንብ አገራችን እንደሚፈነዳ መተንበይ ግን ይቻላል።

አገራችን ላይ ዝቅተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ ያነጣጠረ የቦንብ ፍንዳታ ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ያለ ድርጊት ነው። በርግጥ ወደኋላ ተመልሶ ከምርጫ 97 በኋላ ከተደረጉት ፍንዳታዎችጋር ለማዛመድና ያላቸውን ተመሳሳይነት ለማቅረብ ሁኔታው በተፈጠረ ጊዜ የነበረውን ያገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ከምርጫ 97 በኋላ ከተፈጸሙት ጋር በአግባቡ ማዛመድ ይፈልጋል። ስለዚህም ያን ተጨማሪ መረጃ እስከሚገኝ መሰብሰብ እስክንችል እንተወው። አሁን ባለው ሁኔታ በቅርብ ሚስጥሩን የሚያውቁ እየደፈሩ ስለሆነ ሳንደክምበት መውጣቱ አይቀርም። ነገር ግን ሊሰራበት ሊቆፈር የሚገባው እንቆቅልሽ የቤት ስራችን ነው።

ፈረንሳይ ለጋሲዮን ላይ ሰልፈኞች የጅ ቦንብ ጥለው ሰባት ወታደሮችን ገደሉ ብሎ ይጀምራል። ከምርጫው በኋላ መለስ የመረውን ጭፍጨፋ እንዲመረምሩ ሀላፊነቱን የወሰዱት ግለሰቦች ግን ግኝታቸው ሰልፈኞቹ ከድንጋይ በስተቀር የልታጠቁ እንደነበር ነው። በትክክል እነዛ ወታደሮች በቦንብ ፍንዳታ ተገለው ከነበረ በቀጥታ ለጭፍጨፋው ተጠያቂ ለሚሆነው ለመለስ ዜናዊ ነጻ ባያወጣውም ለመከራከሪያው አስፈላጊ ነው። ነገር ግን የተሰየሙት አጣሪ ኮሚቴዎች በቂ መረጃ በጉዳዩ ላይ እንዲያገኙ ለማድረግ ወያኔዎች አልፈለጉም። እንደውም አጣሪዎቹ ከሁሉም ስራቸው አስቸጋሪ የሆነውና ተድበስብሶ እንዲታለፍ የሆነው የነዚህ ተገደሉ የተባሉ ወደሮች ጉዳይ ነው። ከምርጫው በኋላ ቆየት ብሎ ቢጀምርም ኦሮምያ ክልል ላይ ወደ ሰባት ወር የቀጠለ አመጽ ነበር ስድስተኛው ወር አካባቢ ምእራብ ሸዋ ላይ ያመጹ ተማሪዎች ላይ ቦንብ ተወርውሮ የሞቱ የቆሰሉ ተማሪዎች አሉ። ይህ የቦንብ በቀጥታ ንጽህን ላይ ያነጣጠረ ነው። የቦንብ ጥቃት አመጹን ቀጣይነት እንዳይኖረው አድርጓል። ለነመለስ አመጹን ለማስቆም ጠቅሟል። በዚህ ጉዳይ ላይ የቀረበ ጥፋተኛም የተደረገ አካልም በቀጣይ የተባለበትም ነገር የለም።

ይቀጥልና ከምርጫ በኋላ የነበረውን ሁከት የአጣራው አካል መለስን ለተገደሉት ንጹሀን ተጠያቂ ካደረጉት ጀግናዊ በመረጃ የተደገፈ ምስክርነታቸውን ለህዝባችንም ለአሜሪካን ህዝብ ተወካዮች ካቀረቡ በኋላ መለስ ወደሱማሌ ሊገባ ሲወስን። በዛን ሰሞን ጅማ ላይ በእማኞች መካከል በተሸረበ ተንኮል በደንብ እንዲቀዳ ከተደረገ ዘግናኝ ድርጊት በተጨማሪ አዲስ አበባ ላይ ቦንብ ፈንድቶ ብዙዎችን ገደለ አቆሰለ።

በውጪ ያለው ተቃውሞ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ጊዜና በአንዴ በአለም ዙሪያ የተቀናበረ ሰልፍ በሚደረግበት ጊዜ አገር ቤት መነሳሳትን መፍጠር ሲጀምር ። የሩጫው መድረክ ሁሉ ተቃውሞ ሲሆን አሁንም ቦንብ አዲስ አበባ ላይ ፈንድቶ ብዙ ንጹሀንን ገደለ አቆሰለ።

የቅንጅት መሪዎች ተፈተው ህዝብ ፍጹም የሆነ አብሮነትን ማሳየት ሲጀምር አሁንም ቅንጅት ላይ የነበራቸው ግምት የተሻለ ጠንካራ ሆኖ ይወጣል የሚል ስለነበር አዲስ አበባ ላይ ቦንብ ተጥሎ ብዙሀንን ገደለ አቆሰለ።

አሁን በቅርብ የሱማሌ ሽንፈት ምንም ሊሉበት የማይችሉት ጥርት ያለ ሽንፈት አብሮትም የጦሩን ለምን የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ፤ የአንድነት ፓርቲ መሰረት እየያዘ ከህዝብም መገናኘት ሲጀምሩ፤ የመድረክ መመስረት በአጠቃላይ ተቃዋሚው ጠንከር እያለ መሄድ ሲጀምር። መርካቶ ላይ መለስተኛ ጉዳት ያስከተለ የቦንብ ፍንዳታ ነበር።

ከላይ ጀምረን ካየነው። ፍንዳታዎቹ በሙሉ አገሪቷ ውስጥ የፖለቲካ ውጥረት ባየለባቸው ጊዚያት የተፈጸሙ ናቸው።

ፍንዳታዎቹ በሙሉ መለስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎቻችን የሚበዙባቸው የሚያዘወትሩባቸው ሆቴሎች የትራንስፖርት አገልግሎቶች አካባቢ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። የአላሙዲን ማደያ የተባለው እንኳ ከህንጻው ርቆ መለስተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ ዜጎቻችን ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙበት ናፍጣ መሸጫው ላይ ነው ቦንቡ የፈነዳው። ሰለባዎቹም አዳዩና ተሰልፈው ይገዙ የነበሩ ንጹሀን ናቸው።

ለፍንዳታዎቹ መለስ እንደ ጊዜው የፖለቲካ ሁኔታ የተለያዩ ተጠያቂዎችን ምክንያት ያደረገበት ሁኔታ ነው ያለው። ለፍንዳታዎቹ እንደ መንግስትነቱ መለስ ለመክሰሻ ከመናገር ደረጃ ከዜናነት በዘለለ ቀጣይ በሆነ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ተከሳሾቹ ላይ ማስመስከር የቻለባቸው አንድም ጊዜ የለም።

ለፍንዳታዎቹ በሙሉ ሀላፊነቱን የወሰደ አካል የለም። አርገውት ከሆነ የተከሰሱት አካላት ሀላፊነቱን ሊወስዱ ሲችሉ እንደውም መከሰሳቸውን በአጽኖት የተቃወሙበት ሁኔታ ነው ያለው። የፍንዳታዎቹ ሁሉ ፍጹም ንጹሐን ላይ ያነጣጠረ ባለስልጣኝን አይደለም ተራ ካድሬዎችን ሊጎዳ የማይችል መሆኑ፤ ሊያስገኝ የሚያስችልው ፖለቲካል ወይም ምንም አይነት ጠቀሜታ ለማየት ያስቸግራል። ከነመለስ ውጪ የሚያደርገው አካል ቢኖር በግለሰብ ደረጃ የአይምሮ በሽተኛ የሆነ ግለሰብ የሚያደርገው የሚያስመስል ነው የሚሆነው፡፤

እነዚህንና እየወጡ ያሉ እነመለስ የሚሰሩባቸውን አካሄዶች፤ ችግሮችን ለመወጣት የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች አስፈሪ ነገር ግን የሞኝ የሆኑ የተደጋገሙ ድሪግቶቻቸውን በአጠቃአላይ አስተሳሰባቸውን ላጤነ፤ በቅርብ የተከታተልነውን ቴዲ አፍሮ ላይ የተሰራውን የተቀናበረ ወንጀል አይቶ ቀጣዩን እኩይ ድርጊታቸው ላይ ለርግጠኝነት ቀረበ ግምት ማድረግ ይቻላል።

የአሬናን የትግራይ ላይ ህዝባዊ ስብሰባ፤ በውጪው ያለውን ትግል እየተጠናከረ መሄድ፤ በወ/ሪ ብርቱካን መታሰር ከውጪው አለም እየጎረፈ ያለው ተቃውሞ፤ ገና እየቆየ የሚበስለውን የጦሩንና የነመለስን የሱማሌ ጦስ ግምት ውስጥ በማስገባት ምን አልባት ወደትግራይ ይሻገራል እንጂ ሌላ ንጹሀን ላይ ያነጣጠረ የቦንብ ጥቃት በቅርብ ይኖራል።

ዛሬ ሀያ ነገ አስራምስት እያለ ሰለባ የሚሆኑ ንጹሀን ዜጎቻችን ቁጥር እየበዛ ነው። ማንም አካል በጉዳዩ ላይ ለመናገር በቂ መረጃ ካለማግኘትም፤ እርስ በርስ ካለ ጥርጣሬ፤ ጉዳዩን ከፖለቲካ ውጪ ለማየትም ካለመፈለግ ይመስላል ጉዳዩ የሚገባውን ያህል ትኩረት አልሰጡበትም ወይም መረጃ ቆፍረው ለማጋለጥ የሞከሩ የሉምና ሊታሰብበት ይገባል።

በነዚህ ጉዳዮች ላይ መረጃ ጠቃሚ ሀሳብ ያላችሁ አሁን ካላደረጋችሁት ጥፋቱ ይቀጥላል የብዙዎችን ንጽሀን ሂወት ይቀጥፋልና አቅርቡት። ይህ የቦንብ ጥቃት አጋጣሚ ሰኔና ሰኞ የገጠመባቸው ማንኛችንም ላይ የሚደረግ ስለሆነ የናንተም የኛንም ቤተሰቦች ሰላባ ሊያደርግ የሚችል ነው።

የፖለቲካ ድርጅቶች በይበልጥም ሰቪክ ድርጅቶች መረጃ የመሰብሰብ ሀላፊነት አለባቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በወያኔ እንዲሁም በተለጣፊ ድርጅቶቹ ውስጣዊ አሰራር፤ ከዋናው ተዋናዮች በተጨማሪም አባላቶቻቸው ደጋፊዎች ላይ መአከል ተቋቅሞ ምንም አይነት መረጃዎች መሰብሰብ መጀመር አለበት። መአከሉ መቋቋሙን ይፋ ካደረጋችሁ ሰዎች ያሏቸውን ጠቃሚ መረጃዎች እንዲልኩ ለማግኘትም ጨመር አርገው እንዲያስቡ እንዲሰሩ ያደርጋል። ጠቃሚ ሆኖ ከተገኝ መረጃዎችን መግዛት መጀመር አለብን። ስራው አቅምን አመኔታን እውቅናን ይጠይቃል።

ዳኮታ የጥናት መአከል
Dakota@gafat.com